# 6. መሸጋገሪያ ስልቶች በዘመን ለውጥ እሳቤ በአዊ ዞን በዚገም ማህበረሰብ በደመራ በዓል አከባበር ማሳያነት

*ታሪክ እጅጉ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎቸዎችና ስነፅሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል፣ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ*

Email: ejigutarik@gmail.com

## *አጠቃሎ*

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በዚገም ማሕበረሰብ፤ በደመራ በዓል አከባበር ሥርዓት ውስጥ ለዘመን ለውጥ የሚገለገሉባቸው የመሸጋገሪያ ስልቶች ምን እንደሚመስሉ መመርመር ነው፡፡ ጥናቱን ለማካሄድ መረጃዎች የተሰበሰቡት በቀዳማይና ከካልኣይ ምንጮች ነው፡፡ ቀዳማይ ምንጮች በምልከታ፣ በቃለመጠይቅ፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት ቁልፍ የመረጃ አቀባዮችን በጥናቱ በማሳተፍ የተገኙ ሲሆን፣ በመረጃ ምንጭነት ሴት ሰድስት ወንድ አስራሶስት በድምሩ አስራዘጠኝ ሰዎች ተሳትፈውበታል፡፡ በጥናቱ የተሳተፉ ሰዎች በዓላማ ተኮር የተመረጡት በጉዳዩ ዙሪያ ባላቸው ባህላዊ እውቀት እና ችሎታ ሲሆን፤ በጠቋሚ ናሙና ስልቶች ደግሞ የሌሎችን መረጃ አቀባዮች ጥቆማ መነሻ በማድረግ የተመረጡ መረጃ ሰጭዎች ናቸው፡፡ ከፊል ነጻ እና ውስን ቃለ መጠይቅን በመጠቀም የተሰበሰበው መረጃ በተፈጥሯዊ መቼት በመስክ ላይ በተካሄደ ምልከታና በተተኳሪ የቡድን ውይይቶች ትክክለኛ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ በውይይቱ ተሳታፊ የነበሩ ቡድኖችም ሦስት ናቸው፡፡ በነዚህ ዘዴዎች የተገኘው መረጃ የሚያሳየው ማህበረሰቡ በዘመን ለውጥ ሂደት ውስጥ የመሸጋገሪያ ስልቶችን የሚከውኑት የተለያዩ ቁሳቁሶችን በመጠቀም ሲሆን፤ ተግባሩም አዲስ ዓመትን ለመቀበል በሚደረገው የቅድመ ዝግጅትና በበዓሉ ወቅት እንደሆነ ጥናቱ አመላክቷል፡፡ በመሆኑም፤ በመረጃ ትንተናው የተገኘው ውጤት በደመራ በዓል ሥርዓተ ክዋኔ ሂደት ውስጥ ማህበረሰቡ በዘመን ለውጥ ጊዜ አዲስነት መጎናጸፍ እና ለአምላክ ምስጋና ማቅረብ የመሸጋገሪያ ስልት መሆናቸው፤ ማህበረሰቡ ራሱን፣ አካባቢውን እና ቁሱን ከደዌና ከቆሻሻ በማንጻት የዘመን ለውጥ ማድረጋቸው፤ ክልከላ ያረፈባቸው ነውር የሆኑ ጉዳዮች በመጠበቅ ወደ አዲሱ ዓመት ሽግግር ማድረግ መቻላቸው በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

**ቁልፍ ቃላት፡-** የዘመን ለውጥ፣ሽግግር፣ከበራ፣ጊዜ ሰሌዳ

# 1. መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

የሰው ልጅ በህይወት ዘመን ዑደት ውስጥ ሲኖር የእለት ከእለት እንቅስቃሴውን የሚመራበት የተለያዩ የከበራ ሥርዓቶች አሉት፡፡ እነዚህ፣ ከበራዎች በህይወት ዑደት ውስጥ አስፈላጊ በመሆናቸው፣ የሰዎች እምነት፣ ባህላዊ ፍልስፍና፣ እውቀት፣ አመለካከትና መሰል ጉዳዮች ነጋሪዎችም ናቸው፡፡ ቡድኖች በህይወታቸው ውስጥ ልማዶችን ደጋግመው በመከወን አስፈላጊነታቸውን ይጠቁሙባቸዋል፡፡ በመሆኑም፣ Rappaport, (1992፡252) ከበራዎቹን በህይወታቸው ውስጥ ከሌሎችን በቀጣይነት የማንነታቸው መገለጫ አድርገው፤ ይጠቅሙኛል የሚሏቸው ደግሞ በተለያየ መንገድ እየለወጡ ከህይወታቸው ጋር እያስማሙ ይኖራሉ በማለት ይገልጻሉ፡፡

ለውጥ በህይወት ዑደት ውስጥ በሁነቶች ላይ የሚታይ አይቀሬ ጉዳይ ነው፡፡ የጊዜ እሳቤ የሚገኘውም በህይወት ዑደት ውስጥ በመሆኑ፣ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ቅንጅት ውጤት የሆኑት ሰዎች ለውጥን አጅበው የሚመጡ ሥርዓተ ከበራዎች የሚሸኟቸው አስፈላጊ በሆኑ የእድገት ደረጃዎች ውስጥ ሆነው ነው፡፡ ይህን በተመለከተ፡-R.Canda (1988፡206)[5] ለውጥ በግለሰብም ሆነ በማሕበራዊ የህይወት ዑደት ውስጥ ሥርዓቱን ጠብቆ የሚታይ ከመሆኑም ባሻገር፣ ሰዎች ከቀድሞ ማንነታቸው ወጥተው አንጻራዊ የሆነ እድገት የሚያመጡበት ነው ይላሉ፡፡ በመሆኑም፣ ለውጥ ጊዜን በመመርኮዝ ሂደቱን ጠብቆ በተለያዩ ሁነቶች ውስጥ የሚከሰት አወንታዊና አሉታዊ ምላሽ ያለው ነው፡፡

ሰዎች በተዘረጋው የህይወት ዑደት ውስጥ ሲራመዱ ሁነኛው መሻገሪያ ላይ ለመድረሻቸው፣ ለመቅረባቸውና ለመግባታቸው በማሳወቂያነት የሚጠቀሙባቸው ምልክቶች አሏቸው፡፡ እነዚህ ሁነኛ ምልክቶች ከማሕበረሰቡ እሴት፣ እምነት፣ ደንብ፣ ፍልስፍና፣ ልማድ፣ትውፊት ጋር በእጅጉ የተሳሰሩ ናቸው፡፡ በመሆኑም የዘመን አቆጣጠር ከላይ የተጠቀሱት ምልክቶች ጠቅሎ ከሚይዘው ባህል ይመዘዛል፡፡ ለዚህ ነው ጌታቸው (1993፣20 ዓ.ም) ‹‹የዘመን አቆጣጠር ባህል ወይም ትውፊት ነው›› በማለት የገለጹት፡፡ ዘመንን ለመቁጠር የሚገለገሉባቸው ልማዶች የሚመነጩት

---

[5]*በጥናቱ ውስጥ የተገለጹት የሙህራን ሃሳቦች በአውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር የሆኑት እንዳለ የተቀመጡ ሲሆኑ፣ በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር የተገለጹት ደግሞ ዓ.ም በሚል ተለይተዋል፡፡*

ከማሕበረሰቡ ነው፡፡ በመሆኑም፣ ማሕበረሰቡ ዘመን ለመለካት በኑሮ ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሙት ክስተቶች ምልክት አድርጓል፡፡ ይህን በተመለከተ፡-አብርሃም (2000፣48-49 ዓ.ም) ‹‹ሰዎች የሚደርስባቸው የተፈጥሮ ችግርና የአየር ጠባይ ለውጥ /ብርድና ሙቀት/ ለመከላከል የአኗኗራቸውን እውቀት ለመጠበቅ እንደጊዜው ሁኔታ አስፈላጊውን ጥናት በማድረግ ዘመኑን እየቆጠሩ እየመረመሩ ኑሯቸውን ገፍተዋል፡፡›› በማለት አስረድተዋል፡፡ ስለሆነም፣ እየተተካኩ የሚመጡ ተፈጥሯዊ የሆኑና በሰዎች ላይ አሉታዊ ተጽኖዎችን የሚያስከትሉ ክስተቶች አሉ፡፡

የዘመን ለውጥ በእሳቤው፣ በክዋኔውና በመከሰቻ ጊዜው ከማኅበረሰብ ማኅበረሰብ ይለያያል፡፡ ይህን በተመለከተ፡- ጌታቸው (1993፣19-21ዓ.ም) ‹‹የዘመን ለውጡ በኢትዮጵያን ክርስቲያኖች መስከረም አንድ ቀን ነው›› በማለት ጠቅሰው፤ ለቀኑ መምጣት ምክንያት የሆኑ ተፈጥሯዊ ክስተቶችንም ሲያወሱ፣‹‹የዘመን መለዋወጥ ከከዋክብት በተለይም (ከፕላኔቶች) ሂደት ጋር በተያያዘ የሚከሰት መሆኑ ግልጽ ነው›› በማለት ያስረዳሉ፡፡ Bell (1997፡103) የእስልምና የዘመን ቆጠራ ስሌት መሰረቱ ከሃይማኖቱ ታሪካዊ አመጣጥ ጋር የተያያዘ እንደሆነ በመግለጽ፣ ከመካ ወደ መዲና የተደረገው ጉዞ ወይም ሂጅራ ምክንያት ያደርጋል በማለት ያስረዳሉ፡፡

የተለያዩ የማሕበረሰብ ክፍሎች እንደየፍልስፍናቸውና አመለካከታቸው የዘመን መለኪያ ስልቶች አሏቸው፡፡ ቡድኖች ስልቶችን መነሻ በማድረግ የዘመን ለውጥ የሚያካሂዱት ሁነቶች ታሳቢ ያደረጉ ከበራዎችን ወቅት ጠብቀው በመከወን ነው፡፡ ለውጥን ተከትለው የሚመጡ ከበራዎች የማሕበረሰቡ ህልውና ማስጠበቂያ መሳሪያዎች፣ ጠንካራ ማህበራዊ ትስስርና የአንድነት ስሜት መፍጠሪያ መንገዶች አድርገው የሚመለከቷቸው አሉ፡፡ Segal, (2012፡179-180) ከበራዎች የማሕበረሰቡን ህብረትና አንድነት/unite /፤ ዝናና እርስ በእርስ መግባባትንም / relationships / ጭምር የሚያሳዩ ናቸው በማለት ይገልጻሉ፡፡ እነዚህ ሥርዓቶች ሰፋ ያሉ የተለያዩ እሳቤዎች አቅፈው የመያዝ አቅም ያላቸው ሲሆኑ፣ በቤተሰብ አባላትና በማህበረሰቡ መካከል በንቁ ስሜት ላይ የተመሰረተ ጥልቅ የሆነ ማሕበራዊ ተራክቦ የማጠናከር ሃይል አላቸው፡፡

በተለየ መንገድ የተመለከቱት Thomas (2001:5) ከበራዎች አንድን ክስተት ለመሸኘት፤ አዲሱን በደስታ ለመቀበል ፤የእምነት ሥርዓትን ለማክበር፤ ሀዘንን ለመግለጽ፤ ለሽግግር፤ ለመጽናናት፤ ለአንድነት፤ ለተሀድሶ፤ ለአእምሮ መዛባት ተላልፎ ከመሰጠት እንዲሁም ከሌሎች ጥፋቶች ለመዳን፤ የተለያዩ ግንኙነቶች ለማጠናከር ሲባል የሚከናወኑ ትልቅ ትርጉም የሚሰጣቸው

ተግባራት ናቸው ይላሉ፡፡ ስለዚህ፣ ከበራዎች የሰዎች ማንነት መጠቆሚያ፤ አሉታዊና አወንታዊ ተጽኖዎች ማስገንዘቢያ፤ የማሕበረሰቡን ወይም የቡድኑ የሽግግር ሁኔታን ማሳያዎች ናቸው፡፡

በመሆኑም፣ በእነዚህ የከበራ ሥርዓተ ክዋኔዎች ውስጥ አይቀሬው ጉዳይ የሆነው የሰው ልጅ ሽግግር ነው፡፡ ይህን በተመለከተ፡- Thomassen (2009;6) በህይወት ዑደት ውስጥ ግለሰቡ ወይም ማሕበረሰቡ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ የሚያደርገው ሽግግር/ Transition /ሁነኛና ሊከሰት የሚገባው ጉዳይ መሆኑን በመግለጽ አያይዘውም፣በሥርዓተ ከበራዎች ውስጥ ሶስት የለውጥ ሂደቶች አሉ፡፡ እነሱም፡- መነጠል /Separetion/፣ሽግግር/Transition/፣ቅልቅል /Aggregation/ናቸው በማለት ያስረዳሉ፡፡ ስለዚህ ማህበረሰቡ በህይወት ዑደት ውስጥ ከሚከውናቸው ስርዓቶች አንዱ ከበራ ነው፡፡ በዚህ ሂደት ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ስርዓቱን ተከትሎ በሚመጣው ለውጥ ውስጥ ከአንድ እርከን ወደሌላ እርከን የሚደረገው የመሸጋገሪያ ስልት ነው፡፡

ማሕበረሰቦች ወይም ቡድኖች የሚከውኗቸው የተለያዩ የከበራ አይነቶች[6] አሏቸው፡፡ ከነዚህ ውስጥ አንዱ የሆነው ጊዜ ሰሌዳዊ በዋናነት የሚያጠነጥነው ከወቅቶች ጋር በተያያዘ ነው፡፡ Bell, (1997፡ 103) ጊዜ ሰሌዳዊ አከባበር በወቅቶች መፈራረቅና በነገሮች ትውስታ ይከበራል፡፡ በወቅቶች መፈራረቅ የሚከበሩ በዓላት አዝመራ ሲዘራና አዝመራ ሲሰበሰብ ነው ሲሉ፤ Pentikäinen ,(1997 ፡735) ጊዜ ሰሌዳዊ ከበራ ልዩ ልዩ የሥርዓተ ክዋኔዎችን እንደ አመታዊ በዓላት ወይም ወቅታዊ የሆኑ ስራዎች ዘር መዝራት፣ ምርት መሰብሰብ፣ አዲስ አመት መምጣትንና የመሳሰሉትን ሥነሥርዓት ያካትታል ይላሉ፡፡ Tzanelli,(2011:3932) .ደግሞ ጊዜ ሰሌዳዊ አከባበር ጽንሰ ሀሳቡ የአንድን ግለሰብ ወይም ቡድን ከአንድ ደረጃ ወደቀጣዩ ደረጃ የሚደረገውን

---

[6] *ከበራዎችን Bell(1997;94) በስድስት ከፍለዋቸዋል፡፡ እነሱም፡- የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር* /the rites of passage/*፤ጊዜ ሰሌዳዊ ከበራዎች*/calenderical rites/*፤ የመስዋእት ማቅረቢያ የሚከበር* /rites of exchange and communion/*፤ የስቃይ ስርአት /rites of affiction/፤ ጾምን ተከትለው የሚፈጸሙ*/feasing, fasting and festivals/*የፖለቲካ ስርአተ ከበራዎች/political rituals/ በማለት ነው፡፡ Martha, and Marthin. (2005;110-125)ሲከፍሉ፡- የህይወት ኡደት/rites of passage/ ፤ የእድሜ ሽግግር/age transiton/፤ የተነሳሽ /initiation ritual/፤ የስም አወጣጥ ስርአተ ከበራዎች/ naming ritual/ በሚል በአራት ይከፍላሉ፡፡ Turner, Victor.(1967; 6) የህይወት ኡደት /rites of passage/እና የስቃይ/crisis/ ሲሉ Pentikäinen (1997; 735) ደግሞ የህይወት ውጣ ውረድ/crisis rites/ እና ጊዜ ሰሌዳዊ/calenderical/ ስርአት በማለት በሁለት ከፍለውታል፡፡ በመሆኑም፣ ለዚህ ጥናት የተጠቀምሁት የBell እና Pentikäinen አከፋፈል ነው፡፡ ምክንያቱም፣ ከጥናቱ ርእስ ጋር በእጅጉ የሚቀራረቡት የከበራ አከፋፋል አይነቶች ውስጥ ስለሚመደቡ ነው፡፡*

ሽግግርና ይህን የማንነት ሽግግር ተከትሎ የሚመጡ የተለያዩ ሥርዓቶች ያጠቃልላል በማለት ይገልጻሉ፡፡

ስለዚህ፣ ሰዎች በህይወት ዑደት ወስጥ የተለያዩ ከበራዎችን የሚከውኑት ወቅቶችን ጠብቀው ነው፡፡ የሥርዓቱ መከወኛ ጊዜ የባህሉ ባለቤት በሆኑት ማሕበረሰብ ዘንድ ይታወቃል፡፡ በተለይም ደግሞ በጊዜ ሰሌዳዊ ክብረበዓላት ላይ የሚስተዋሉት ቀጣዩን ምዕራፍ የሚጠቁሙ እንዲሁም፣ የዘመን መለወጥ የሚያመላክቱ ልማዶች ናቸው፡፡ ለውጡም ተፈጥሯዊ ሂደት ተከትሎ የሚከሰት ነው፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በዚህ ርዕስ ላይ እንዳተኩር የተለያዩ ምክንያቶች አነሳስተውኛል፡፡ የመጀመሪያው ምክንያት የዚገም. ባህልና ቱሪዚም መጽሄት (2009፣4ዓ.ም)፡፡ እንደሚያብራራው የደመራ በዓል አከባበር ስርዓተ ክዋኔ ካሉት የአዊ ዞን ወረዳዎች ውስጥ በተለየ ሁኔታ ትውፊታዊ ስርዓት በመከተል የማህበረሰቡ ባህልና ማንነት በመጠበቅ እየተከበረ በርካታ ጊዜያት በማስቀጠር እስካሁን ድረስ ቀጥሏል ይላል፡፡

በመሆኑም፤በ2004 ዓ.ም በዓሉ በዚህ ቦታ በተለየ ሁኔታ ስለሚከበር በዞኑ ባህልና ቱሪዝም እንዲሁም፣ ኮምኒኬሽን መምሪያዎች በጋራ ባዘጋጁት ፕሮግራም ከምሰራበት ተቋም ተጋብዤ ወደ ቦታው የመሄድ እድል አጋጥሞኝ ነበር፡፡ በወቅቱ በዓሉ ሲከበር በመድረክ ከወረዳው አስተዳዳሪ፣ ከባህልና ቱሪዚም ጽ/ቤት ሃላፊ እንዲሁም፣ ከቤተ-ክህነት ሰዎች የደመራ አከባበር ሥርዓቱን አስመልክቶ የተለያዩ ሃሳቦች ለታዳሚዎች ይወሳሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት የከበራ ስር ዓቱ በተለየ ሁኔታ መከበር በዝርዝር ለመዳሰስ ሲባል ይህ ጥናት እንዲጠና ሆኗል፡፡

ሁለተኛው ምክንያት በበዓሉ የጉብኝት ወቅት የህጻናት ጸጉር መላጨት፣ የምግብ ዝግጅታቸው፣ የመመገቢያ ጊዜያቸው፣ቅቤ በምሰሶ እና በምሳና ግንድ ላይ ማስቀመጣቸው ነው፡፡ ማህበረሰቡ እነዚህን ሁነቶች የሚከውኑት በዘመን ለውጥ እሳቤ ውስጥ ሁነው ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ ሽግግር ለማድረግ የሚያስችላቸው እንደሆነ ማዳመጤና መመልከቴ ትኩረቴን የሳቡት ጉዳዮች ናቸው፡፡ ስለዚህ እነዚህ ምልከታዎች በተጨባጭ በጥናት በዝርዝር ለማየት ሲባል የጥናቱ አነሳሽ በመሆን ቀርቧል፡፡

በተጨማሪም፤ ኪዳነማሪያምና ሌሎች (1988፣33 ዓ.ም) የአዊ ማህበረሰብ የተለያዩ በርካታ ባህላዊ እሴቶች ባለቤት ነው። ነገር ግን የነዚህ እሴቶች ባለቤት ቢሆንም ሙህራን ጥናትና ምርምር ለማድረግ ፊታቸውን ብዙም ወደአካባቢው እስካሁን አላዞሩም በማለት ይገልጻሉ። በሌላ መንገድ በአዊ ዞን በተለያዩ ቦታዎች የተጠኑ ጥናቶች አሉ፤ የሺ ደምሴ (2011ዓ.ም) በጓንጓ ወረዳ በጥሩብርሃን ቀበሌ ማሳያነት፤ ስመኝ ይሁን (2011ዓ.ም) በአንከሻ ጓጉሳ ወረዳ በሶስቱ ግምጃ ቤት ቀበሌ፤አዲሱ የኔሁን (2005 ዓ.ም) በጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ የመስቀል በዓል አከባበር ሥርዓተ ክዋኔ በተመለከተ የተጠኑ ናቸው። በጥናቱ ውስጥ የተተነተኑት ሃሳቦች የመስቀል በዓል የቅድመ ዝግጅት፣የበዓሉ እለት እንዲሁም ድህረ የበዓሉ ስርዓተ ክዋኔ በስሱ ለመተንተን ተሞክሯል።

በእነዚህ ጥናቶች የተመለከትሁት ክፍተት፤ ርዕሱ የመስቀል በዓል አከባበር ሥርዓት የሚል በመሆኑ፤ ከመስቀል ጋር በተያያዘ የሚነሱ ሃይማታዊ ጉዳዮች ላይ በማተኮር የተሰሩ ናቸው። ነገር ግን በአዊ ዞን ዚገም ወረዳ የደመራ በዓል አከባበር ስርዓተ ክዋኔ ውስጥ ያሉት የመሸጋገሪያ ስልቶች ከዘመን ለውጥ አንጻር በሰነድ ተሰንዶ ለትውልድ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ በተገቢው ሁኔታ በሙህራንና በባለሙያዎች ተጠንቶ አይገኝም። በመሆኑም፤ይህ ጥናት በያዘው ርዕስ ዙሪያ ከአዊ ባህል አንፃር የዚገም ማሕበረሰብ የዘመን እሳቤ በማንሳቱ የመጀመሪያ በመሆኑ አነሳሽ ምክንያት ሆኖኛል።

### 1.3. የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአዊ ዞን በዚገም ማሕበረሰብ፤ በደመራ በዓል[7] አከባበር ሥርዓት ውስጥ የመሸጋገሪያ ስልቶች በዘመን ለወጥ እሳቤ ምን እንደሚመስሉ መርምሮ ማሳየት ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች አሉት፡-

---

*[7] የደመራ ምንነትን በተመለከተ ቃሉን በቁሙ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (1948፣353) የበዓለ መስቀል ዋዜማ እንጨቶች የሚደመሩበት ሲሉ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል (1993፣456) ደግሞ 1.መስከረም አስራ ስድስት ቀን የሚከበር የመስቀል በዓል ዋዜማ 2. ከላይ የተጠቀሰውን በዓል አስመልክቶ በሥነ ሥርዓቱ ላይ እንዲነድ የሚደረግ የእንጨት ቁልል፣ ስብስብ ይሉታል፡፡*

*፣አቡነ ገሪማ (2000፣46 ዓ.ም) የደመራ በዓል ንግስት ኢሌኒ መስቀሉን ከተቀበረበት ለማውጣት ኪራኮስ በተባለ አንድ አረጋዊ አማካኝነት የተሰጣትን ጥቆማ መሰረት በማድረግ እንጨት ሰብስበሽ ከምረሽ እጣን አፍስሽበት ጭሱ ከላይ ወጥቶ ወደ ታች ሲመለስ አቅጣጫውን አይተሽ አስቆፍሪ በተባለችው መሰረት መስቀሉን አውጥታዋለች ይላሉ፡፡ ደመራ የሚደመረው ይህን ለማስታወስ ነው፡፡*

*መስቀል የሚለው ቃል በርካታ ትርጓሜዎች አሉት፡፡ አቡነ ጎርጎሪስ (1991፣97) መስቀል የኖህ መርከብ የተሰራችበት እንጨት፤ ሙሴ የፈርኦንን መሰግላን ድል ያደረገበት በትር ምሳሌዎች ናቸው፡፡ ምእመናን በመስቀል አምነው አማትበው ከሀጥያት፣ ከአምልኮ ጣኦት ድነዋል፡፡ መስቀል ኢጋንትን፣ መናፍቃንን፣ ፍትወትን ድል ያደርጋል፤ በማለት በእጅ የሚያዘው፣ በአንገት የሚደረገው መስቀል ያለውን ሃይል ይገልጻሉ፡፡ ለመስቀል ይህ ሁሉ ሃይል የተሰጠበት ምክንያት ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት በመሆኑ ነው፡፡ ንግስት እሌኒ በእየሩሳሌም ደመራ ደምራ ያስወጣችው መስቀል*

- ለዘመን ለውጡ የሚያገለግሉ የመሸጋገሪያ ስልቶች ተምሳሌታዊ ውክልና መተንተን፡-
- በከበራ ሥርዓቱ ሂደት የሚከወኑ የሽግግር ስልቶች የሚያሳዩ የመንጻት እሳቤዎች መፈተሽ፡-
- የዘመን ለውጥ የመሸጋገሪያ ስልቶችን ክዋኔ መተንተን የሚሉት ናቸው፡፡

### 1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት

- የአካባቢው ማሕበረሰብ ከትውልድ ትውልድ ሲያስተላልፉት የቆዩት ባህላዊ የዘመን ለውጥ እሳቤ እውቀታቸውን ወደፊት ለማስቀጠል በጽሁፍ መልክ ተሰንዶ መቀመጡ ማሕበረሰቡ በዘመን ሂደት ያሉበትን ደረጃ ለመረዳት ያስችላቸዋል፡፡
- ስለ አካባቢው ማሕበረሰብ በፎክሎር ጥናት ውስጥ ባህላዊ የዘመን ለውጥ ሽግግር በተመለከተ ያለውን የመረጃ እጥረት በመቅረፍና ለአጥኚዎችና መሰል አካላት በማድረስ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

### 1.5. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ከይዘት አንጻር በደመራ በዓል አከባበር ሥርዓት ውስጥ የመሸጋገሪያ ስልቶች በዘመን ለወጥ እሳቤ ምን እንደሚመስል መመርመር ላይ አተኩሯል፡፡ ምክንያቱም፣ይህን ሃሳብ መመልከቱ ስለተጠኚው ማህበረሰብ ባህልና ወግ እንዲሁም የአኗኗር ዘይቤ በቂ የሆነ ግንዛቤ ስለሚሰጥ ነው፡ ከቦታ አንጻር፣ ያተኮረው በአዊ ዞን ውስጥ ካሉት ወረዳዎች በዚገም ማሕበረሰብ ውስጥ ባሉ ሁለት ቀበሌዎች ሲሆን፣ ወረዳውን የመረጥሁት የበዓሉን ባህላዊ ትውፊት በሚገባ አገኝበታለሁ ብየ በማሰብ ነው፡፡

## 13. የምርምር ዘዴዎች

### 2.1. የመረጃ አቀባዮች አመራረጥ ዘዴ

ተጠኝዎች የተመረጡበት የናሙና ዘዴ አላማ ተኮር /Purposive sumpling/ና ጠቋሚ የናሙና አመራረጥ /snow balling/ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች በአላማ ተኮር የተመረጡት፤ ጥናቱ በደመራ በዓል አከባበር ሥርዓት ውስጥ የመሸጋገሪያ ስልቶች በዘመን

---

*ደግሞ ይህ ነው፡፡ በመሆኑም፣ አማኞች መስቀል የድህነታቸው ምሳሌ በመሆኑ ሃማኖታዊ አስተምህሮውን ተከትለው የመስቀል በዓል ያከብራሉ፡፡ በተጨማሪ፣ ሐመር መጽሄት (1994፣11) መስቀል ለአማኞች ደህነት፣ ትዕምርት፣ መመኪያ፣ ሃይል ነው፡፡ በመሆኑም፣ የመስቀል በዓል በማክበር፣ በመመስከር፣ በመሳለም፣ በማማተብ... ለመስቀል ያላቸውን ክብር ይገልጻሉ ይላል፡፡ ስለዚህ፣ ይህን ክብር ለማግኘት በዓሉን ያከብራሉ፡፡ ይህ ጥናት ግን ከመስቀል መከበር ምክንያት ጋር በተያያዘ ያለውን ሃይማታዊ ሥርዓት ሳይሆን ከደመራው ሥርዓት ጋር ተያይዞ የሚፈጸሙ የማሕበረሰቡ ልማድ በማጥናት ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡*

ለወጥ እሳቤ ምን እንደሚመስል መመርመር ላይ የተመሰረተ በመሆኑ፣ ዓላማው መሰረት ተደርጎ በጉዳዩ ዙሪያ መረጃ ኑሯቸው ሊሰጡ የሚችሉ ወካይ ተሳታፊዎች ከጊሳይታና ዲሂ ቀበሌዎች መምረጥ ስላስቻለ ነው፡፡ በተጨማሪም፣ ጠቋሚ ናሙናን /snow balling/ የተጠቀምኩት ደግሞ ቀዳሚ መረጃ አቀባዮች ከኔ የተሻለ ሰው አለ ብለው ሲጠቁሙ ሌሎች መረጃ አቀባዮች ለማግኘት ስላገዘ ነው፡፡ ስለዚህ፣ ሁለቱ የናሙና የመምረጫ ዘዴዎች በመጠቀም ሴት ስድስት ወንድ አስራ ሶስት በድምሩ አስራ ዘጠኝ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ሲመረጡ፣ ንዑሳን የመረጃ አቀባዮች ደግሞ ወንድ አምስት ሴት ሁለት በድምሩ ሰባት ሰዎች ተመርጠዋል፡፡ የተመረጡት ሰዎች ያላቸው ባህላዊ እውቀት፣ጾታና እድሜ የመምረጫ መስፈርት በመሆን አገልግሏል፡፡

## 2.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

በዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች የተሰበሰቡት በምልከታ፣በቃለመጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት ዘዴዎች ነው፡፡ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ምንነት ከዚህ በታች በሰፊው ተብራርተዋል፡፡

### 2.2.1.ምልከታ

ማሕበረሰቡ ለደመራ በዓል አከባበር ሥርዓተ ክዋኔ የሚያስፈልጉ የሚቆረጡ ምሳናዎችና የተለያዩ የበዓሉ ማድመቂያ ቁሶች በመረጃነት መሰብሰብ የሚቻለው በማየት፣በመስማትና ሌሎች የስሜት ህዋሳትን ጭምር በመጠቀም ነው፡፡ ስለሆነም፣ በቦታው በአካል በመገኘት ራሴን ከማሕበረሰቡ ጋር በማዛመድ በአውዱ ንቁ ተሳታፊና ኢ-ንቁ ተሳታፊ በመሆን መረጃዎችን መሰብሰብ ችያለሁ፡፡ በመሆኑም፤በቅድመ ዝግጅት ምዕራፍ ወቅት የምሳና ግንድ በመላጥና በመቁረጥ፣ ቅቤ ወደምሰሶ መወርወርና ግንድ ላይ ማስቀመጥ በጾታ፣ በእድሜና በማሕበራዊ ደረጃዎች ልዩነት ምክንያት ክዋኔውን የመጋራት እድል ባለማግኘቴ ኢ-ንቁ ተሳታፊ ሆኛለሁ፡፡ የእርቅ ስርዓት መከወን፣ የምግብ ዝግጅት፣ የንጽህና ተግባራት ላይ ተሳታፊ በመሆን የሰበሰብኳቸው መረጃዎች ነበሩ፡፡ በዚህ ወቅት በፎቶ ግራፍ፣ በቪዲዮ ካሜራ እና በፅሁፍ ማስታወሻ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

### 2.2.2. ቃለ መጠይቅ

ስለጉዳዩ የበለጠ እውቀት፣ልምድ ያላቸው እንዲሁም፣ ጾታና እድሜን መሰረት በማድረግ የተመረጡ መረጃ አቀባዮች ቅቤ ምሰሶና ጉሚቲ ላይ ማስቀመጥ፣ የምግብ መመገቢያ ጊዜ…ላይ ያላቸው አመለካከት በተመለከተ ነጻ ቃለመጠይቅ እንዲሁም፤ የእርቅ ሥርዓተ ክዋኔ፣የምግብ አዘገጃጀት የንጽህና ትርጓሜ ወይም ተምሳሌታዊ ፍች በውስን ቃለመጠይቅ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ቃለመጠይቅ የመጠቀም  ምክንያት በምልከታ የማይገኙና ግልጽ ያልሆኑ መረጃዎች ለማሟላት ነው፡፡

### 2.2.3. ተተኳሪ የቡድን ውይይት

ተተኳሪ የቡድን ውይይት ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በመሆን የተመረጠ ሲሆን፣ ዘዴው ጥቅም ላይ የዋለው በሌሎች ዘዴዎች ያልተሰበሰቡ መረጃዎች ለማግኘት፣ተጠኝው ማሕበረሰብ ያመነባቸውና የተስማማባቸው ሃሳቦች ለማግኘት፣ከመረጃ አቀባዮች የተለያየ ምላሽና የሚጣረሱ አጠራጣሪ መረጃዎች ለማረጋገጥ እንዲሁም የቡድኑ ባህላዊ እውቀት ለመመርመር የሚያስችል ዘዴ በመሆኑ ተጠቅሜበታለሁ፡፡ ስለሆነም፤ ስለደመራ በዓል ሥርዓተ ክዋኔ ባህላዊ እውቀት ያላቸው ሰዎች እንዲሁም፣ ጾታን ያማከለ መስፈርት በማዘጋጀት ሶስት ቡድን ተዋቅሯል፡፡

## 2.3. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

ከመስክ በምልከታ፣ በቃለመጠይቅና በተተኳሪ የቡድን ውይይት ዘዴዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች በባህሪያቸውና በአይነታቸው በማደራጀት አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ በመጠቀም፣ የመሸጋገሪያ ስልቶች በዘመን ለውጥ እሳቤ ምን እንደሚመስል ያለው ትርጓሜ ለመተንተን ተጠቅሜበታለሁ፡፡ ምክንያቱም ርእሰ ጉዳዩ ገለጻን የሚጠይቅ ስለሆነ ነው፡፡

## 2.4. የንድፈ ሃሳብ ማእቀፍ

በተለያዩ መንገዶች የተሰበሰቡት መረጃዎች በየፈርጁ ተደራጅተው ተስማሚ ከሆኑ ቲዮሪዎች አኳያ መታየት እንዳለባችው Marshal & Rossman (2006:156)ና Creswell 2007:161) ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም፤በዚህ ጥናት ውስጥ በልዩ ልዩ ዘዴዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች የትዕምርቶች መፈከሪያ ንድፈ ሀሳብ /Symbolic Interpretations theory/ በመጠቀም ታይተዋል፡፡፡፡

እንደ Dorson (1972:55) አከፋፈል ትዕምርቶች "ቁሳዊ ባሕል" በሚባለው የፎክሎር ዘውግ ሥር የተነሱ ናቸው፡፡ሃሳቡን በመጋራት Turner,(1961:76) 'ትዕምርቶች የማሕበረሰብን እውቀት ያቀፉ

እሴቶች ናቸው’ ይላሉ፡፡ በመሆኑም፣ ማሕበረሰቡ በደመራ በዓል ጊዜ በባህላቸው እየተመሩ የሚከውኗቸው ተግባራት ከቁሶች ጋር የተቆራኙ ናቸው፡፡ ትርጓሜያቸውም የሚገለጸው ቁሱ በያዘው ማሕበረሰባዊ እሳቤ ነው፡፡ ማሕበረሰቡ እንዲፈጸም የሚፈልገው ግለሰባዊ፣ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ፣ጉዳዮች በቁሶች በመወከል ከበራዎችን ይከውናሉ፡፡

ባህላዊ ቁሶች ቁሳዊ መገለጫ ብቻ ሳይሆኑ ያላቸው ረቂቅ የሆኑ እሳቤያዊ ትዕምርት ጭምር ናቸው፡፡ቁሱ ባዘለው ሁለንተናዊ ጉዳይ ውስጥ፤ በቅርጹ፣ (ክብ፣ ድቡልቡ፣ ጎድጓዳ…)፣ በቀለሙ (ቀይ፣ጥቁር፣ነጭ)፣ ቁሱ በተሰራበት ጥሬ እቃ (እንጨት፣ አፈር፣ ድንጋይ…) በድምጾች የመሰሚያ ጊዜ ( ሌሊት፣ ጠዋት፣ ምሽት…)፣ አቅጣጫ ጠቋሚ ክስተቶች (ምስራቅ፣ ምእራብ፣ ወደቀኝ፣ ወደ ግራ…) የመሳሰሉት ትዕምርቱ የሚገለጽባቸው ጉዳዮች ሆነው ይመጣሉ፡፡

ትዕምርት የሚገለጸው ከላይ በተጠቀሰው መንገድ ብቻ ሳይሆን በተግባርም ሊገለጽ እንደሚችል Turner (1967; 19) ሲገልጹ፡- ትዕምርቶች ውጫዊ ወይም ግኡዝ በሆነው ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የሚገለጹት ሰዎች በሚከውኗቸው ተግባሮች ውስጥ ተምሳሌታዊ ጉዳዮች እንዳሉ ያስረዳሉ፡፡ አክለውም ከቁሱ ባለፈ አካላዊ እንቅስቃሴዎች፤ ማሕበራዊ ተግባቦቶች፤ የተለያዩ ተግባሮች፤ ምልክቶችና ቦታዎች የትዕምርት እሳቤዎች የተሸከሙና ልዩ የሆኑ በከበራ ውስጥ የሚስተዋሉ ጉዳዮች እንደሆኑ ይገልጻሉ፡፡

በአጠቃላይ የቁሳዊ ባህሎች ትዕምርት የሚገለጸው የባህሉ ባለቤት በሆነው ማሕበረሰብ ነው፡፡ ተገላጭ ነገሮችም የማሕበረሰቡ ባህላዊ እውቀት፣ ፍልስፍና፣ እምነትና አመለካከት የተሸከሙ መሆናቸው በማሕበረሰቡ ውስጥ የጠበቀ ትስስር ይፈጥራሉ፡፡ ይህን በተመለከተ Bell (1997:61) ትዕምርቶች የቡድኑ የጠበቀ አንድነት ለማሳየት፣ ለመጠበቅና ለማቆየት ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ በማለት ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም፣ ጥናቱን መነሻ አድርገው የተሰበሰቡ መረጃዎችም ባመዛኙ ከሚያሳዩት ቅርፅ፤ ቀለም፤ ተግባርና እረቂቅ እሳቤ አንጻር ያላቸው ትርጓሜ የትዕምርቶች መፈክሪያ ንድፈ ሀሳብ /Symbolic Interpretations theory/ በመጠቀም ታይተዋል፡፡

## 3. የመረጃ አቅርቦት፣ትንተናና ትርጎማ

በዚህ ክፍል የተሰበሰቡ መረጃዎች ከጥናቱ አላማዎች አኳያ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

### 3.1. ለዘመን ለውጡ የሚያገለግሉ የመሸጋገሪያ ስልቶች ተምሳሌታዊ ውክልና

ማሕበረሰቡ የዘመን ለውጥ የሚያደርገው በዘፈቀደ ሳይሆን በተቀመረ እውቀት ላይ ተመስርቶ ነው፡፡ ይህ እውቀቱና ልምዱ የተገኘው ከተከማቸው የማሕበረሰቡ ህግ፣ደንብ፣ እሴትና ልማድ ነው፡፡ ሥርዓተ ከበራዎች ለውጥ ተከትለው በመምጣት በሰዎች አማካኝነት እውን ይደርጋሉ፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ እንደከበራው አይነት የዘመን ሽግግር እሳቤው ተግባራዊ የሚሆንበት የራሱ ስልት አለው፡፡

### 3.1.1. ፀጉርን መላጨት

የደመራ በዓል የሚከወነው ሰፊ ጊዜ ተይዞለት ነው፡፡ ይህም የቅድመ ዝግጅት ጊዜ፣ የበዓሉ እለትና ዋዜማ ናቸው፡፡ የጸጉር መላጨት ሥርዓት ተግባራዊ የሚደረገው በበዓሉ የቅድመ ዝግጅት ምእራፍ ላይ ባሉት ቀናት ሲሆን፣ የሚላጩት ህጻናትና ለአቅመ ሂዋን የደረሱ ሴቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ሴቶች የጸጉር መላጨት ሥርዓቱ እንደእድሜ ደረጃቸው የሚለያይ ቢሆንም፣ አላማው ግን ወደቀጣዩ እርከን መሸጋገርን መሰረት ያደረገ ነው፡፡

ማንኛውም ሰው ተፈጥሮ ያደለችው የራሱ የሆነ ስጦታ አለው፡፡ ከስጦታዎች ውስጥ ቀዳሚ የሰው ልጅ ልብሶች ጸጉር፣ ጥፍርና ቆዳ ናቸው፡፡ እነዚህ ሁነቶች መላጨት፣ መቁረጥና ማጠብ የተለያዩ አውዳዊ ትርጓሜዎች ያስገኛሉ፡፡ በዚህ ጥናት ጸጉር መላጨት፣ ከአንድ እርከን ወደሌላኛው ለመሸጋገር የሚያስችል ስልት ሲሆን፣ በማሕበረሰቡ ዘንድ ጸጉር በቅድመ የከበራ ሥርዓት ወቅት አለመላጨት የአዲስ ዓመት ተስፋዎች ለማግኘት ዝግጁ አለመሆናቸውን ያሳያል፡ ፡ ይህን በተመለከተ ደሳለው ይሁን (19/01/2011ዓ.ም በተካሄደ ቃለ መጠይቅ)‹‹አዲስ ዓመት ሊመጣ ሲል ህጻናትና የደረሱ ሴቶች ይላጫሉ፡፡ ባህል ነው፡፡ ካልተላጩማ ችግር ነው፡፡ ያ ሰው የኛን ባህል የሚከተል አይደለም፡፡ አዲስ ዓመት በደስታ መቀበል አይችልም፡፡ ችግሩ ዓመቱን ሙሉ አብሮት ይኖራል፡፡ ስለዚህ፣ ከዚህ ለመዳን ይላጫል›› በማለት ያስረዳሉ፡፡ ማሕበረሰቡ የጸጉር መላጨት ሥርዓት የሚከውነው አዲስ ዓመት ለመቀበል በሚደረገው የቅድመ ዝግጅት ሂደት ወቅት ነው፡፡ በመሆኑም፣ ከለውጥ ደረጃዎች ውስጥ በመካከለኛው የሽግግር ጊዜ ከሚከሰቱ ክስተቶች ውስጥ ጸጉር መላጨት አንዱ ነው፡፡ ይህ ክዋኔ ወደአዲሱ ማሕበራዊ ሥርዓት ሊያደርስ የሚችል የመሸጋገሪያ ስልት በመሆን ለማሕበረሰቡ የዘመን ለውጥ ለማድረግ የሚያስችል ተግባር ነው፡፡

መላጨት የመሸጋገሪያ እርከን እንደሆነ የገለጹት ዋልተንጉሥ (2007፣217) ‹‹ከአንዱ የህይወት እርከን ወደሌላኛው የህይወት እርከን ሽግግር ስናደርግ ከቀዳሚነት የሚያሸሽ ሥራ እየፈጸምን

እንዜዳለን፡፡ አንድን ደረጃ አጠናቅቀን ሌለኛውን ስንጀምር ተፈጥሯችንንለመምሰል ሁሉም ነገር በአዲስ እንዲበቅልና እንዲወጣ፣ ህይወት በአዲስ ኃይልና ጉልበት እንዲጀምር ለማድረግ እንሞክራለን›› ይላሉ፡፡

በመሆኑም፣ ዘመን ለመሻገር አዲስ ጸጉር ማብቀልና መላበስ የማሕበረሰቡ ባህላዊ ግዴታ ነው፡፡ በዚህ መንገድ ቀሪው ለማለቁ መጭው ለመጀመሩ ጥቁምታ የሚሰጥ የመሸጋገሪያ ድልድይ ነው፡፡ አዲስ የሆነ ጸጉር ማውጣት (ማብቀል) በተመለከተ ቄስ ሽባባው አሊ (17/01/2011ዓ.ም በተካሄደ ቃለ መጠይቅ) ‹‹ተላጭተው አዲስ ጸጉር ነው የሚያወጡት፡፡ ያ ሚሆነው ወደአዲሱ ዘመን ንጹህ ሆኖ አዲስ ጸጉር ማብቀል አዲስ ዘመንን ያሳያል፡፡›› ይላሉ፡፡

ከላይ ካሉት መረጃዎች የሚስተዋለው በዚገም ማሕበረሰብ ዘንድ መላጨት ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ የሚደረግ የሽግግር ጉዞን ያሳያል፡፡ ክዋኔው በአዲስ ዓመት የቅድመ ዝግጅት ጊዜ መሆኑ ወደቀጣዩ እርከን ለመድረስ የሚያስችል ተግባር ሆኖ ይመጣል፡፡ አዲሱን ዓመት ለመቀበል የሚያስችል የዝግጅት ጊዜ መሆኑ፣ ጉዳዩን የዘመን ለውጥ እሳቤ እንዲጋራ አድርጎታል፡፡ የጸጉር መላጨት ሥርዓት ውስጥ ሽግግር አለ፡፡ ምክንያቱም፣ የዘመን ለውጡን ምክንያት በማድረግ የሚላጭና በአዲስ ዓመት የቅድም ዝግጅት ጊዜ የሚከወን ተግባር መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

### *3.1.2. ስጦታ ማቅረብ*

ሰጦታ፣ የሆነን ጉዳይ ምክንያት በማድረግ ለተለያዩ አካላት በስጦታ መልክ የሚበረከት ወይም የሚቀርብ ነው፡፡ ማሕበረሰቡ የዘመን ለውጥ ሲያደርግ ከዘመን ዘመን ያሻገረውን አምላክ ለማመስገን ሲል የተለያዩ ስጦታዎችን ለአምላኩ ያቀርባል፡፡ ይህን ተግባር በደመራ በዓል አከባበር ሥርዓት ላይ በመከወን ያሳያል፡፡ በምልከታ በተረጋገጠውየዚገም ማሕበረሰብ ችቦን በበዓሉ ዋዜማ ዕለት በምሰሶ ያስራል፡፡ መጀመሪያ ላይ ያሰረውን ብትን ችቦ ምሰሶ ላይ ከታሰረው የባላቶች[8] እንጨት ጋር አቀራኝቶ ሲያስር ሚስትም ከባለቤቷ ጎን ሁና ጠጀሳር፣ አደይአበባና ሌሎችንም ቅጠሎች በማሰር ስጦታ ታቀርባለች፡፡ ይህን ሲከውኑ‹‹መጭው ጊዜ የምርትና የደስታ ዘመን ይሁንልን›› እያሉ እየመረቁ ነው፡፡ተምሳሌታዊ ውክልናውበምርቃኑ ምክንያት ዘመኑ ወደፊት የሰላምና የምርት እንዲሆን የሚያስችል ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

---

[8] *ቃሉ የአዊኛ ቃል ሲሆን ፤ብዙ ባላዎች ያሉት ፣ቅርፊቱ የተላጠና ቀለሙ ነጭ የሆነ ከምሳና እንጨት የሚዘጋጅ ለደመራ በዓል አከባበር ስርዓተ ክዋኔ የሚያገለግል እንጨት ነው፡፡*

ምሰሶ ላይ የሚታሰር ችቦ ማሕበረሰቡ የተለያዩ ውክልናዎች በመስጠት ያለውን ትልቅ ክብር ይገልጽበታል። አቶ ፈንታሁን ይስማው(16/01/2011ዓ.ም በተካሄደ ቃለ መጠይቅ) ሲገልጹ፡- ‹‹መጀመሪያ ‹የዛሬ አመት በሰላም አድርሰን› ብለን አምላክን እንለምናለን። የመጀመሪያው ችቦ የሚታሰርበት ምሰሶ በዚህ ሰዓት እንጨት አይደለም። እግዚሀር ነው። አባወራ እማወራ ማለት ነው። አንዳች ነገር የሚወጣው የሚወርደው በምሰሶ ነው። የአምላክ ምህረትም የሚወርደው በምሰሶ ነው። የእግዚሀር ቁጣም የሚመጣው በዚሁ ነው››። በማለት ያብራራሉ። ምሰሶ አምላክንና የቤተሰብ አስተዳዳሪ የሆኑት እናትና አባት ወክሎ የሚገኝ ቁስ ነው። ይህን ውክልና ተሸክሞ የተገኘው ሁሉንም ማድረግ የሚችል ስለሆነ፣ በቤት ውስጥ ያለው ማንኛውም የሚበላ የሚጠጣና እንዲሁም፣ ሌሎች ቁሶች መጀመሪያ ለምሰሶ በስጦታ ይቀርባሉ። ስጦታው የሚቀርበው ዘመኑ የሰላም፣ የምርት እንዲሆን ከመመኘት ባለፈ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ የመሸጋገሪያ ስልት በመሆን አገልግሏል።

## ግንድ ወደ ቤት ማስገባት

ተቆርጦና ተልጦ አስራ ሶስት ግንድ ይዘጋጃል። የተዘጋጀው ግንድ ወደ ቤት ማስገባት ለዘመን ለውጥ ሂደቱ ማሳያ ሁኖ ይመጣል። ግንድ ወደቤት የሚገባው በበዓሉ ዋዜማ በአስራ ስድስት ምሽት አካባቢ ነው። አቶ ጉልላት አደያም የዘመን ሽግግርን በተመለከተ ሲገልጹ፡- ግንዶቹ ምሽት ወደ እሳቱ ሲጨመሩ፣ወደቤት የሚመጣው ዘመድ አዝማድ ድሩፃ[9] ሲል የቤቱ ባለቤትና እቤት ታድመው የተቀመጡ የበዓሉ ተሳታፊዎች ደግሞ መቶ ሺ አመት ያድርስህ እያሉ የሚመጡ ሰዎችን ሁሉ ይቀበላሉ። በመቀጠልም ቅቤው ግንዱ ላይ ሲቀባ፣ ቅቤው በምሰሶ ገበታ ላይ ሲወረወር፣ የተቀጣጠለው ችቦው በደመራ ላይ ሲጨመር...፤በሰፈሩ የተከበሩ አዛውንት የዛሬ አመት በሰላም ያድርሰን፣ከብቶችን፣ ልጆችን፣ ሰብሉን፣ አምላክ ጠብቆ ከዘመን ዘመን ያሻግርልን እያሉ ይመርቃሉ በማለት ያስረዳሉ።፡- ከዚህ ሃሳብ መረዳት የሚቻለው ማህበረሰቡ ለዘመን ለውጥ የሚጠቀሙባቸው የተለያዩ ለመሸጋገሪያነት የሚያገለግሉ የማብሰሪያ ቃሎች በመጠቀም የዘመን ሽግግር ማድረጋቸው ነው።

በተጨማሪ አቶ ፈንታሁን ይስማው (16/01/2011ዓ.ም በተካሄደ ቃለ መጠይቅ) ሲገልጹ፡-‹‹ከቤቱ ደጃፍ ላይ የሚሰደረው ነጭ ግንድ አስራ ሶስት ሲሆን፤ግንዱ ነጭ መሆኑ ብርሃን ያሳያል።

---

[9] ቃሉ የአውኝ ሲሆን ትርጓሜውም እንኳን አደረሳችሁ እንደማለት ነው

በአዲሱ ዓመት ብርሃን እቤታችን ይግባ ስንል ግንዱን ከደጃፍ እንሰድራለን፡፡ ወደቤት የሚገባው አስራሁለት ግንድ ነው፡፡ አንዷ እውጭ ትቀራለች፡፡ ግንዶች የአስራሁለት ወራት ምሳሌ ሲሆን፣ አንደኛዋ ጳጉሜ ወር ናት››፡፡ በማለት ያብራራሉ፡፡ ትዕምርት የሚገለጽባቸው መንገዶች ውስጥ አንዱ የቁሱ ቀለም ነው፡፡ በበዓሉ ዋዜማ ከውጭ ተደርድረው ወደቤት የሚገቡት ግንዶች ቀለማቸው ነጭ መሆናቸው፣ብርሃንን የሚወክሉ ናቸው፡፡

ስለዚህ፣ ተሻግረው የሚያገኙት ዘመን የሰላምና የብርሃን ዘመን እንዲሆንላቸው ግንዱን ይልጣሉ፡ ፡ የግንዶቹ ቁጥር ደግሞ በዓመቱ ውስጥ ያሉ ያአስራሶስት ወር ምሳሌ ናቸው፡፡ በተጨማሪ ትዕምርቶች የቡድኑን የጠበቀ አንድነት ለማሳየት፣ ለመጠበቅና ለማቆየት ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ግንዱ የሚገባው በተናጠል ሳይሆን ሁለት ሰዎች በአንድ ላይ ነው፡፡ ጥንድ ሁነው ማግባታቸው፣ በግንዱ አማካኝነት መያያዛቸው አምላክ ሁሉንም ሳይለያይ በአንድነት ጠብቆ ከጨለማውና ከጭቃው አውጥቶ ብርሃን ለማየት መድረሳቸው፣ ሞት በመሃከላቸው ገብቶ ሳይነጣጥላቸው ወደአዲሱ ዓመት ለመሻገር መምጣታቸውን እንዲሁም፣ የማሕበረሰቡ የመተጋገዝና የመረዳዳት ባህሉ ጠንካራ መሆኑን የሚገለጽበት የመሸጋገሪያ ስልት ነው፡፡

### 3.3 የእርድ ስርዓት መከወን

በአስራሰባት የበዓሉ እለት የተለያዩ ተግባራት ይከወናሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ በዋናነት የእርድ ስርዓተ ክዋኔ በዋናነት የሚጠቀስ ነው፡፡ የእርድ ስርዓት የሚከወነው በአስራስድስት ተደምሮ ካደረው ማህበረሰቡ በጋራ ደመራ በሚያቃጥሉበት ቦታ ላይ ለእርድ የተዘጋጀው በግ፣ ፍየል፣ በሬ እንደሁኔታው እንስሳቱ ለእረድ ይቀርባሉ፡፡ በዚህ ወቅት ታላላቅ ሽማግሌዎች ከመረቁ በኋላ እርዱ ይከወናል፡፡ በእርድ ስነስርዓቱ ጊዜ የሚፈሰው ደም በማህበረሰቡ ዘንድ ተምሳሌታዊ ውክልና አለው፡፡ ይህን በተመለከተ ቄስ ዘገየ ወርቁ (17/01/2011 በተካሄደ ቃለመጠይቅ) እርድ ለአዊ ህዝብ ትልቅ ትርጉም አለው፡፡ የመጀመሪያው ካለፈው ዘመን ወደ አዲሱ ዘመን ለመሻገር ማብሰሪያ ከመሆኑ በተጨማሪ ቁመን ለምንሄድበት፣ደመራ ላነደድንባት መሬት ካሳ ነው፡፡ ሌላውና ዋናው ጉዳይ ግን ከእርድ በኋላ ለሚመጣው አመድ አጥፊ ዝናብ እንደማምጫም ይወሰዳል፡፡ዝናቡ ዘንቦ አመዱን ካጠፋው የምርት ዘመን ነው፡፡ያ ካልሆነ ግን ዘመኑ ያስፈራል፡፡ በማለት ያስረዳሉ፡፡ ከላይ ካለው ሃሳብ መረዳት የሚቻለው እርድ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚከወነው በዘመን ሽግግር ሂደት አዲሱ ዘመን ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር የሚያስችል መሆኑን ነው፡፡

## 3.2. በከበራ ሥርዓቱ ውስጥ የሚከወኑ የሽግግር ስልቶችን የሚያሳዩ የመንጻት እሳቤዎች

ትዕምርቶች ውጫዊ ወይም ግኡዝ በሆነው ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የሚገለጹት ሰዎች በሚከውኗቸው ተግባሮች ውስጥ ተምሳሌታዊ ጉዳዮች ይንጸባረቃሉ፡፡ በማሕበረሰቡ ዘንድ መንጻት በተለያየ መንገድ ይታያል፡፡ በከበራ ሥርዓቱ ውስጥ የሚከወኑ የመንጻት እሳቤዎች ሽግግር የሚያሳዩ ሲሆኑ፣ ገላን መታጠብ፣ ልብስንና እቃን ማጠብ፣ አካባቢ ማጽዳት፣ ምግብ ማዘጋጀት፣ ከተጣሉት ጋር እርቅ መፈጸምና ሌሎች ተግባራት በመከወን ማህበረሰቡ ከምንም ነገር ጸድቶ ለአዲሱ ዘመን ዝግጅት ያደርጋል፡፡ ይህ የሚደረገው አካባቢን ከተለመደው ደዌ፣ ቆሻሻና ከቂም በቀል አንጽቶና አጽድቶ ከአንዱ እርከን ወደሌላው እርከን ሽግግር ሲደረግ ለውጡ የሚበሰርባቸው መንገዶች መሆናቸውን ለማብሰር ነው፡፡

### 3.2.1. በማጽዳት መንጻት

ውሃ በከበራ ሥርዓቱ ውስጥ የሚገኝ አንድ አላባ ነው፡፡ ዋልተንጉሥ (2007፣232 ዓ.ም) እድፍን ከአካል፣ አካልን ከእድፍ የሚለይ መንጽሒ ነው ብለው ይገልጹታል፡፡ ውሃ ቆሻሻን አስወግዶ ንጽህናን ያስገኛል፡፡ ይህን በተመለከተ አቶ ሙልጌታ አለማየሁ (02/13/2011ዓ.ም በተካሄደ ቃለመጠይቅ) ‹‹መስከረም ጠዋት ወፍ ሳይጮህ ወንዝ ሄደን ገላችንን እንታጠባለን፡፡ በዚህ ጊዜ ውሃው እንደ ጸበል ይቆጠራል፡፡ በክረምት ወራት የለበስነው ልብስ ጭቃ፤ውሃ ነው፡፡ መስከረም ሲጠባ እንጸዳለን፣ ህመም አይጣበቅብንም፣ ሰው ከሰው ይገናኛል፣ መንገዱ ነጻ ይሆናል፤ ይህ ጊዜ ለኛ የብርሃን አመት ነው›› ይላሉ፡፡ በተጨማሪም የደመራ በዓል ስርዓተ ክዋኔ የቅድመ ዝግጅት ስራ የሚጀምረው ከመስከረም አንድ ጀምሮ ነው፡፡ በመሆኑም፤የመንጻት ተግባር ከዚህ ጊዜ ይጀምራል፡፡ ሙልጌታ አለማየሁ (02/13/2011ዓ.ም በተካሄደ ቃለመጠይቅ) ይገልጻሉ፡፡

ከደዌና ቆሻሻ የሚጸዱት ወደቀጣዩ ደረጃ ሽግግር ለማድረግ ነው፡፡ ማሕበረሰቡ ይህን መንጻት የሚያመጣው የወንዝ ውሃ ለእጥበት በመገልገል ሲሆን፣ ማንኛውንም ደዌና ቆሻሻ ይዞ ፍሰቱ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በማድረግ ይወርዳል፡፡ ምዕራብ የምስራቅ ትይዩና የጸሃይ መግቢያ በመሆኑ መጥፎውን ሁሉ ወደጨለማውና ጥልቁ ለመስደድ፣ ለማራቅ ወንዝ ላይ እጥበት ይከውናሉ፡፡ በሌላ መንገድ ማሕበረሰቡ ከስጋ ደዌ ለመንጻት ሲባል ‹‹የጳጉሜ ወር ውሃ›› እንዳያልፈን በሚል ወንዝ ወርዶ ገላውንና ልብሱን ይታጠባል፣ያጥባል፡፡ ደዌው በጸበሉ ይነጻል በዚህ መንገድ ወደ ቀጣዩ እርከን ይሻገራል፡፡

ንጽህና በደመራ በዓል የቅድመ ዝግጅት ወቅት ከሚከወኑ ሥርዓቶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ቄስ ዘገየ ወርቁ (02/13/2011ዓ.ም በተካሄደ ቃለ መጠይቅ)‹‹መስቀል ሊደርስ አካባቢ ሁሉንም ልብስ እናጥባለን፡፡ የምንለብሰው ነጭ ነው፡፡ እስከ ወንዝ ድረስ መንገዱን እንጠርጋለን፡፡ የቤት እቃ፣ ጠቀርሻ ሁሉ የዛን ግዜ በውሃ ይጸዳል፡፡ ልክ እንደቆሻሻው አሮጌውን ዘመን ትተን በንጽህና የብርሃኑን ዘመን ለመቀበል ዝግጅት እናደርጋለን›› ይላሉ፡፡ በመሆኑም፤ ማሕበረሰቡ ያለበትን አላስፈላጊ የሆነ ግሳንግስ ሁሉ በማጽዳት ወደአዲሱ ዓመት ንጹህ ሆኖ ለመሸጋገር በተለያየ መንገድ ዝግጅት ያደርጋል፡፡ ይህ የዝግጅት ተግባር አንዱ የመሸጋገሪያ ስልት በመሆን የዘመን ለውጡን ነጋሪ ሁኖ ይመጣል፡፡

### 3.2.2. በማቆያ ቦታ መንጻት

የዚገም ማሕበረሰብ ከአለፈው ዘመን ወደአዲሱ ዘመን ሽግግር ሲያደርግ ንጽህና መሰረታዊ ጉዳይ ሆኖ ይመጣል፡፡ ንጽህና በተለያየ መንገድ የሚገለጽ ቢሆንም፣ በዚህ ክፍል ለማየት የተፈለገው በቁስ አማካኝነት የሚገለጸውን ንጽህና ነው፡፡ ለደመራ አገልግሎት የሚውለው የምሳና እንጨት በቅድመ ዝግጅት ምእራፍ ጊዜ ተቆርጦ እስከ በዓሉ ዋዜማ የሚቀመጠው ንጽህናው በተጠበቀ ቦታ ነው፡፡ አቶ አሸናፊ መኮነን (10/01/2011ዓ.ም የተካሄደ ቃለ መጠይቅ) የደመራ በዓል ከመድረሱ በፊት ሙሉ በሚባሉት ቀናት (ማክሰኞና ሀሙስ) እየተጠበቀ ግንዱ እየተቆረጠ ተደርድሮ ይቀመጣል፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያት ለንጽህናው ሲባል ሲሆን የደመራ ዋዜማ እስኪደርስ ድረስ ቀደም ሲል በተቆረጠበት ቦታ ይቆያል፡፡ ከዋዜማው በፊት ቀድሞ ወደቤት ቢመጣ ህጻናት፣እንስሳትና ሰዎች ሊያቆሽሹት ስለሚችሉ ንጽህናው እንዲጠበቅ በማቆያ ቦታው ይቀመጣል፡፡ ምክንያቱም ንጹህ ሆኖ ዘመንን መቀበል አስፈላጊ ስለሆነ ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡
ግንዱ የሚቆረጥባቸው ማክሰኞና ሃሙስ (ሙሉ ቀኖቹ) ሲሆኑ ይህ መሆኑ ዘመኑ ምርት፣ ሰላም፣ጤና፣በረከት የሞላበት ይሆናል በሚል ነው፡፡ ንጽህና በማሕበረሰቡ ዘንድ ትልቅ ትርጉም አለው፡፡ ካለፈው ዓመት ወደአዲሱ ዓመት ሽግግር ሲያደርግ ሀብቱ ከየትኛውም ቆሻሻ ጸድቶ መሆን አለበት፡፡ በንጹህ ቁስ የሚከወነውን ተግባር የሚያመልኩት አምላክ ይቀበለዋል፡፡ ስለዚህ፣ የመንጻት ሥርዓቱ የሚከወነው ወደአዲሱ ዓመት ሽግግር ለማድረግ ነው፡፡

### 3.2.3. በምግብ[10] መንጻት

[10]. *በዚህ ጥናት ለማህበረሰቡ መንጻትን የሚያመጡ ምግቦች ከበርበሬ የሚዘጋጅ ለጉዝጉዝ የሚሆን አዋዜና ጠላ ናቸው፡፡*

በምግብ መንጻት ማለት ለከበራ ስርዓቱ አገልግሎት የሚሰጡ ምግቦች ለበዓሉ በሚመጥን የምግብ አቀራረብና አዘገጃጀት ስርዓት በመከተል ቡድኑ ካላስፈላጊ ደዌና ግሳንግስ በመንጻት የዘመን ሽግግር ማድረግ ነው፡፡ይህ እሳቤ በተለያዩ ቁሶች ላይ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

ምግብ በሚዘጋጅበት ወቅት ንጹህ ሆኖ ነው፤ አለበለዚያ የበዓሉ ዕለት ለጤና አይስማማም በማለት ወ/ሮ ገነት አማረ (12/06/2011ዓ.ም በተካሄደ ቃለ መጠይቅ)‹‹ለጉዝጉዝ[11] የሚሆን ንጹህ ዛላ በርበሬ እንደቁሳለን፡፡ አምላክም ይቀበለናል›› በማለት ያብራራሉ፡፡ ይህን ሃሳብ በማጠናከር ወ/ሮ እብስቴ አድማስ (27/06/2011ዓ.ም በተካሄደ ቃለመጠይቅ) ‹‹አዋዜ ከቀይ ሽንኩርትና ከዝንጅብል ይዘጋጃል፡፡ ጨው አሞሌ ነው የሚሆነው፡፡ ነጭ ሽንኩርትና የፈረንጁ ጨው አይፈለግም፡፡ አምላክ አይቀበለውም፡፡ ለጉዝጉዝ የሚሆነው አሞሌ የሚመጣው ንጹሁ ከመሬት ተቆፍሮ ነው፡፡ ሰው እንኳ ሲታመም እቤት ባይኖር ከመንደር ተፈልጎ ነው በዝንጅብል ተደርጎ የሚሰጠው፡፡ ለጤና መዳህኒት ነው፡፡ የተቀደሰ ጨው ነው›› በማለት ያስረዳሉ፡፡

መረጃው የሚያሳየው በምግቦች ላይ የቅድስና፣ የንጽህናና የጤና እሳቤዎች አሉበት፡፡ ይህ ተግባር የሚከወነው በቅድመ ዝግጅት ወቅት ነው፡፡ በመሆኑም ማሕበረሰቡ የበዓሉ ዕለት የሚቀርበው ምግብ ለአምላክ የሚቀርብ መስዋዕት እንደሆነ አድርገው ስለሚያስቡ ንጹህና ቅዱስ መሆኑ ይመረጣል፡፡ ለሰዎችም ጤና እንዲሆን ይፈልጋል፡፡ በዚህ መንገድ ማህበረሰቡ አስፈላጊ ሁኖ የተገኘው ሁሉ በማጽዳት ወደቀጣዩ የዘመን እርከን ሽግግር ያደርጋሉ፡፡

ሌላው በቅድመ ዝግጅት ወቅት ሴቶች ምንጊዜም ቢሆን ጠላ ይጠምቃሉ፡፡ እማወራዋ ጠላውን የምታዘጋጀው በአዲስ መልክ ነው፡፡ ከዚህ በፊት የተጠመቀ ጠላ ቢኖር ያ ጠላ ተወግዶ እቃው በደንብ ታጥቦ አለያም ሌላ ጋን ተፈልጎ በአዲስ ብቅልና ጌሾ ተዘጋጅቶ ይጠመቃል፡፡ ወ/ሮ አስካለች አለም (12/06/2011ዓ.ም በተካሄደ ቃለ መጠይቅ)‹‹እኛ ለደመራ የቆየ ጠላ አናቀርብም፡፡ ቤቱም፣ አባወራውም ሁሉም ደስ አይላቸውም፣ አምላክ አይቀበልም፡፡ ብቅሉን ጌሾውን ክረምት ስለሆነ፣ አስቀድሜ አዘጋጅቼ፣ አድርቄ አስፈጫለሁ፡፡ የቆየ ጠላ አለ ግን ሌላ ጋን አለ በዛ ሌላ ሽቲቲ[12] ነው ለደመራ ያዘጋጀሁ፡፡ አምላክም የቆየውን አይወድም፡፡ እኛም ለአዲስ ዓመት ስለሆነ

[11] ድርብ ከሆነ እንጀራ የሚዘጋጅ የተደቆሰ በርበሬ(አዋዜና) በዛ ያለ ቅቤ ተዋህደው በተደራረበው እንጀራ ላይ ቅቤው ይፈሳል፡፡ የቅቤውን መብዛት ለመግለጽ ሲባል ምግቡ ጉዝጉዝ በመባል ይገለጻል፡፡ ወ/ሮ ገነት አማረ (12/06/2011ዓ.ም በተካሄደ ቃለ መጠይቅ)

[12] የጠላ ጥንስስ

ሁሉንም እንደገና እናዘጋጃለን››ይላሉ። ስለዚህ፣ ሴቶች በአስራ ሰባት ለሚከበረው ደመራ የሚሆን ጠላ በቅድመ ዝግጅት ወቅት ቀድመው ያዘጋጃሉ።

ይህን ሃሳብ በመጋራት አቶ ጉልላት አደያም (12/06/2011ዓ.ም በተካሄደ ቃለ መጠይቅ) ‹‹ሴቶች ቀድመው ሽቲቲ ያዘጋጃሉ። የጠላ ዝግጅት የሚደረገው ከነሃሴ ጀምሮ ነው። ከጉም፣ ከጭቃ፣ ከዝናብ ታግላ ለአዲስ ዓመት ሌላ ሽቲቲ ነው የምታዘጋጀው›› በማለት ሃሳቡን ያጠናክራሉ። ማሕበረሰቡ ከአሮጌው ዘመን ተነጥሎ ወደአዲሱ ዓመት ሽግግር ሲያደርግ በእነዚህ እሳቤዎች የተቃኙ ምግቦች መመገቡ ለህይወቱ ቅድስና፣ ንጽህናና ድህነትን ያስገኝለታል። የዘመን ለውጥ ሲያደርግ ከላይ የተዘረዘሩት ክዋኔዎች በመፈጸም ከነበረበት የአኗኗር ዘዬና ማንነት ተነጥሎ በመውጣት ወደቀጣዩ እርከን ሽግግር ያደርጋል። ስለዚህ፤ምግብ የማንጻት እሳቤ በመያዝ እንደአንድ የመሸጋገሪያ ስልት በመሆን ያገለግላል።

### 3.2.4. በእርቅ መንጻት

እርቅ ሁለት የተለያዩ አካላት ወይም ቡድኖች በድንበር፣ በነፍስ ግድያ፣ በስርቆትና በሌሎችም ምክንያቶች በመካከላቸው የሚፈጠር አለመግባባት በመቅረፍ መፍትሄ የሚገኝበት መንገድ ነው። የእርቅ ሥርዓትን ተግባራዊ ማድረግ በማሕበረሰቡ ዘንድ የመንጻት እሳቤ አለው። እርቅ በማሕበረሰቡ ዘንድ በደመራ በዓል የቅድመ ዝግጅት ወቅት የሚከወን ተግባር ሲሆን፣ ቡድኑ ከየትኛውም ቂምና በቀል ነጻ ሆኖ ዓመትበዓሉን ለማክበር ሲባል ተግባሩ ይከወናል። ለዚህ ምክንያቱ በዓሉ የሚከበረው በተናጠል ሳይሆን በጋራ መሆኑ ነው። በአንድነት ለማክበር ደግሞ የተጣሉት መታረቅ አለባቸው። ወደአዲሱ ዓመት ቂምና ተንኮል ይዞ መሻገር ስለማይቻል ከምንም ነገር ነጽቶ የዘመን ሽግግር ማድረግ እንዳለበት ቡድኑ ያምናል።

አብሮ መብላትና መጠጣት ባህሉ በሆነ ማሕበረሰብ ውስጥ የደመራ በዓል ግለሰቡ ብቻውን ሆኖ አያከብርም። በአቅራቢያው ካሉት ጎረቤቶቹ ወይም ዘመዶቹ ጋር በጋራ በመሆን ነው። ቄስ አደያም ሀረገወይን (02/13/2011ዓ.ም በተካሄደ ቃለ መጠይቅ) ‹‹እርቅ ከብዙ ነገሮች ሁሉ መከልከልና መጽዳት ነው። ጠብ ካለ ባላጋራውን ለማጥፋት፣ ለመግደል፣ ለመበደል ለብዙ ነገር ይፈልገዋል። እርቅ ከተፈጸመ ግን ክፉ አሳቢው ከዚህ ሁሉ ነጻ ይሆናል። ቂም ሀጥያት ነው። ከዚህም ይነጻል። ሌላው በዓሉን በአንድነት ነው የምናከብረው፣ ቂማቸው በእርቅ ተፈቶ ቀጣይ የሚመጣውን አዲስ ዓመትሲያከብሩለሁሉም ይስማማል›› በማለት ሃሳባቸውን ይገልጻሉ።

የተጣሉ ሰዎች እርቅ ሳይፈጽሙ አዲሱን ዓመት አያከብሩም በማለት የገለጹት አቶ የኔሰው አምሳሉ (02/13/2011ዓ.ም በተካሄደ ቃለ መጠይቅ) ‹‹የደመራ በዓል ሲከበር እርቅ በዚገም አዊዎች ባህል አይቀርም፡፡ ምክንያቱም፣ ቂም ይዞ ወደአዲሱ ዓመት መሻገር አይቻልም፡፡ በደመራ በዓል ጊዜ ሁሉም ነገር ንጹህ መሆን አለበት›› በማለት የላይኛውን ሃሳብ ያጠናክራሉ፡፡ ከመረጃዎቹ መረዳት የሚቻለው ከቂም መጽዳትን ነው፡፡ ማሕበረሰቡ ለበዓሉ ካለው ክብር የተነሳ ከሁሉም በላይ መንጻት የሚለው ጉዳይ መሰረታዊ ነው፡፡ በመሆኑም፣ ሰዎች ሲታረቁ በውስጣቸው ያለው ቂም ይሽራል፣ ይጸዳል ተብሎ ስለሚታሰብ የተጣሉ ሰዎችን በማስታረቅ ወደአዲሱ እርከን ለመሻገር ቀድሞ መንጻት የሚለው እሳቤ በማሕበረሰቡ ዘንድ የመሸጋገሪያ ስልት ሁኖ ያገለግላል፡፡ ስለዚህ፣ በዘመን ለውጥ ሂደት ውስጥ አዲሱን ዓመት ለመቀበል የሚያስችል የቅድመ ዝግጅት ሂደት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

## 3.3. ነውርን በመጠበቅ የሚከወኑ የዘመን ለውጥ የመሸጋገሪያ ስልቶች

ነውር (Taboos) Newton (1912፡89) ነውር ሰዎች አንዳንድ ነገሮች ወይም ድርጊቶች እንዳይከውኑ መከልከል፣ ማገድ፣ መርገም ነው በማለት ገልጸውታል፡፡ ነውር በዚህ ጥናት እንዳይከወኑ የተከለከሉ ጉዳዮችን የሚመለከት ሲሆን፣ ማሕበረሰቡ ከደመራ በዓል በፊት በቆሎ እንዳይበላ ክልከላ ያደርጋል፡፡

### 3.3.1. ነውር በመሬት ልጅ

መሬት ዘር ትቀበላለች ምርት ትሰጣለች ከምትሰጣቸው የተለያዩ ሰብሎች ውስጥ በቆሎ አንዱ ነው፡፡ የክረምቱ ወቅት፣ በጋ ላይ የከረመው እህል የሚያልቅበት፣ አዲሱ ለመድረስ ገና የሚያሸትበት ስለሆነ፣ ማሕበረሰቡ ክረምቱን በተለያዩ ችግሮች ካሳለፈ በኋላ የሚደርስ እህል ነው፡፡ ቡድኑ በከበራ ሥርዓቱ የሚደግፈውን ነገር ከማክበር በተቃራኒው የሚወገዘውንና የሚጠላውን ነገር ደግሞ በዚያው ልክ ይገልጽበታል፡፡ በመሆኑም፣ በቆሎ እሸት በማሕበረሰቡ ዘንድ ከደመራ በዓል በፊት ቢደርስም አይበላም፡፡ በዚህ ወቅት መብላት እንደነውር ስለሚቆጠር አይጠቀሙም፡፡

ቡድኑ በቆሎ መብላት የሚጀምረው በደመራ በዓል ዋዜማ እለት (በአስራ ስድስት) እሳቱ ውስጥ በገባው ግንድ ላይ በመጥበስ ነው፡፡ አቶ የኔሰው አምሳሉ (16/01/2011ዓ.ም በተካሄደ ቃለ መጠይቅ) ‹‹በቆሎ ቀድሞ ቢደርስም የምንበላው ከደመራ በዓል ጀምሮ ነው፡፡ ከዛ በፊት አይበላም፡

፡ ነውር ነው። በቆሎ፣ አሾተሪ የተለያዩ እህሎች ደርሰዋል።ራብ በዚህ ጊዜ የለም ። በነውር የተከለከለ ነገር ከደመራ በፊት ቢበላም እህሉ በረከት ያጣል። ልጆች እንኳ ቢበሉ ይታመማሉ። የተዘራ እህል የደረሰበት፤ያለቀበት ላይ እህል የወጣበት ጊዜ ነው››። ይላሉ።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ቄስ አደያም ሀረገወይን(16/01/2011ዓ.ም በተካሄደ ቃለ መጠይቅ) ‹‹በቆሎ እህል እስከሚደርስ ያቆየናል።ደመራ ለኛ ትልቅ ክብር ነው። ወፎችም እህላህሉን የሚነክሱበት፣ ንቦችም አበባዎችን የሚቀስሙበት ጊዜ፣ሰዎችም እሸታሸቱን የሚቀምሱበት፣ የሚበሉበት ወቅት ነው። ከዋዜማ በፊት ግን በቆሎ ቢደርስም አንበላም። የሚበላ ሰው ካለ እንደነውርኛ ስለ ሚቆጠር፣ደፍሮ የሚበላ የለም›› ይላሉ።

ማሕበረሰቡ የዘመን ለውጥ ከሚያደርግበት ቁስ ውስጥ አንዱ የበቆሎ እሸት ነው። ወደአዲሱ ዓመት ሲሻገር በአዲስ ካሸቱት እህሎች ውስጥ በቅድሚያ ያገኘው የእህል አይነት ነው። ከመበያ ጊዜው ቀድሞ ቢደርስም በማሕበረሰቡ ዘንድ ነውር ስለሆነ አይበላም ምክንያቱም፣ ለተለያዩ ችግሮች ስለሚያጋልጥ ከዚህ ለመግታት ሲባል ነውሩ የመከልከያ ስልት ሁኖ ይመጣል። በሌላ መንገድ ሌሎች እህሎች ከመድረሳቸው በፊት የሚገኝ ሰብል ስለሆነ፣ የበቆሎ እሸት ወደቀጣዩ እርከን መሸጋገሪያ ሁኖ ያገለግላል። በዚህ መንገድ ማሕበረሰቡ ከነበረበት ደረጃ ወደሌላው ደረጃ ሽግግር በማድረግ የዘመን ለውጥ እሳቤውን እውን ያደርጋል።

### 3.3.2. ነውር በላም ልጅ[13]

ቅቤ በማሕበረሰቡ ዘንድ የራሱ የሆነ ትርጓሜ አለው። ከዚህ ባሕላዊ ትርጓሜ አንጻር ለተለያየ ተግባር ይጠቀሙበታል። ቅቤን በበዓሉ ወቅት አለመጠቀም ለቡድኑ ነውር ነው። ስለዚህ፣ ማህበረሰቡ ለተለያዩ ቁሶች ይገለገልበታል

ቅቤ በተለያየ ቦታ ላይ ይደረጋል። የመጀመሪያው፣ በምሰሶ ትክክል እሳት ውስጥ ከገባው ግንድ ላይ ይቀባል፣ ሁለተኛው፣ ከምሰሶው አናት ላይ ይወረወራል። ከዚህ የተረፈው ከቤተሰብ አባላት ራስ ላይ ይቀባል። ይህ መሆኑ ለአባወራው፣ ለቤተሰቡና ለእንስሳት ደህንነት የራሱ አውንታዊ አስተዋጽኦ አለው ብለው ያምናሉ። አቶ አዲሱ ተፈራ (12/06/2011ዓ.ም በተካሄደ ቃለ መጠይቅ) ሲገልጹ፡- ‹‹ለምሰሶው አምላክ መስዋዕት በማቅረብ አምላኩን የሚለምንበት ነው። ልመና ለኛ በጎ ነው። የለመነ፣ የጸለየ፣ የተማጸነ የልፋቱን ዋጋ ያገኛል። ስለዚህ፣ሌላው ነገር ሁሉ ቀምሶ

---

[13] *በማሕበረሰቡ ዘንድ የላም ልጅ የሚባለው ወተትና የወተት ተዋጽኦዎች ናቸው:: በመሆኑም፣ በዚህ ጥናት ቅቤን ለመግለጽ የላም ልጅ የሚለውን ሃረግ ተጠቅሚያለሁ::*

ለምሰሶ ሳይወረወር አይቀርም ነውር ነው። ለምሰሶ መወርወሩ ከክፉ ነገር እንድንጠበቅ የአምላክ መለመኛ ነው። ያ ነው ጥቅሙ››ይላሉ። ይህን ክዋኔ በመከወን ማሕበረሰቡ ይታወቃል።
በተጨማሪም፣ ከመጥፎው ነገር ለመዳን ሲባል ተግባሩ እንደሚከወን የገለጹት አቶ አዲሱ ተፈራ (12/06/2011ዓ.ም ቡድን ተኮር ውይይት) ‹‹ቅቤው ግንዱ ላይ ስናደርግ ለዛሬ አመት በሰላም አድርሰን፣አመቱን የሰላም አድርግል እያልን እንመርቃለን። ቀቤውም አብሮ እንደሳት ይነዳል። የሚነደው እሳት በሽታ የሚያመጡ ነገሮችን ሁሉ ያቃጥላል። ስለዚህ ከብቱና ልጁን ከበሽታና ከቸነፈር ይድናሉ። ሌላው ከምሰሶ ላይ ያለ ቅቤ በጢስ ሲመታ ወደታች ይንጠበጠባል። በረከቱን እግዚያብሄር እንደዚህ ቅቤ አውርድልን ስንል ነው›› ከዚሁ ጋር በተያያዘ ቄስ አደያም ሀረገወይን (16/01/2011ዓ.ም ቡድን ተኮር ውይይት)። ‹‹እግዚአብሄር በምሰሶ ይመሰላል። ስለዚህ፣ በረከቱን ለእህሉ ይሰጥልን ዘንድ መለመኛ ነው። ሁላችንም ብንሆን ቅቤ ለምሰሶ ሳንወረውር አንቀርም። ክዋኔው ካልተከወነ ለአምላክ የሚቀርበው መሰዋት የከለከልን ያህል ነው። ለምሰሶ ካልተወረወረ ጎረቤቱም ያነውራል››ይላሉ።

መረጃው የሚያሳየው የአስራ ሁለት ወራት ምሳሌ ከሆነው ግንድ፣ምሰሶና ልጆች ላይ ቅቤውን ማድረጋቸው ምርቱ እንዲባረክ፣ እንስሳው እንዲረባ፣ ልጆች ጤናቸው እንዲጠበቅ መለመኛ ስልት መሆኑ ነው። ስለዚህ፣ቡድኑ ምሰሶን ለሚወክለው እግዚያብሄር መለመኛ የሚሆን መስዋዕት በማቅረብና ነውር በመጠበቅ፣በአዲሱ ዓመት መልካም ነገር ለማግኘት ተስፋና ምኞቱን የሚያሳካበትና ወደቀጣዩ ደረጃ የሚሸጋገርበት ስልት በመሆን ያገለግላል።

## 4. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት አላማ በአዊ ዞን በዚገም ማሕበረሰብ አስተሳሰብ፣ ዕውቀትና ፍልስፍና በደመራ በዓል አከባበር ሥርዓት ውስጥ የመሸጋገሪያ ስልቶች በዘመን ለወጥ እሳቤ ውስጥ ምን እንደሆነ መመርመር ነው። ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ መረጃዎች ተሰብስበው በዓይነታዊ የምርምር ዘዴ ተተንትነዋል። በመሆኑም፤ጥናቱ በመረጃ ትንተናው ሶስት ውጤቶች አመላክቷል። የመጀመሪያው በዘመን ለውጥ ጊዜ አዲስነት መጎናጸፍ እና ለአምላክ ምስጋና ማቅረብ የመሸጋገሪያ ስልት መሆናቸው። ሁለተኛው ማህበረሰቡ ራሱን፣አካባቢውንና ቁሱን ከደዌና ከቆሻሻ በማንጻትና በመተግበር የዘመን ለውጥ ማድረጋቸው፤ሶስተኛው ክልከላ ያረፈባቸውን ነውር የሆኑ ጉዳዮችን በመጠበቅ ወደ አዲሱ ዓመት ሽግግር ማድረግ ናቸው።

## 5. የይሁንታ ሀሳብ

ከጥናቱ ውጤት በመነሳት የሚከተሉትን የይሁንታ ሃሳቦች ማስቀመጥ ተችሏል።

- ባህላዊ የዘመን ለውጥን ምክንያት በማድረግ የሚከወኑ የንጽህና ተግባራት ተጠናክረው የሚቀጥሉበትን ሁኔታ ለማዳበር፤ የጤና ተቋማት እና መሰል ድርጅቶች በባለቤትነት ጉዳዩን ይዘው መስራት ቢችሉ፤
- የአዊ ዞን ባህልና ቱሪዝም እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው ተቋማት ይህን ባህላዊ የዘመን ለውጥ እሳቤ በመቀመር ወደተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች በማስፋፋት፤ ለቱሪስት መዕስብነት በመገልገል የአካባቢውን ማህበረሰብና የሀገርን ገቢ ማሳደግ ቢቻል መልካም ነው።

## ዋቢ መጽሃፍ


በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት እና ምርምር ማዕከል።(1993)።መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

አቡነ ገሪማና ሌሎች።(2000)።የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ልደተ ክርስቶስ እስከ 2000 ዓ.ም። ሜጋ ማተሚያ ድርጅት ታተመ።

አቡነ ጎርጎሪዮስ።(1991)። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ።አዲስ አበባ፣ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ።

አብርሀም ጤናው።(2000)።አቡሻኽር የኢትዮጵያ የዘመን ቀመር ባህረ ሃሳብ። ጎንደር ማተሚያ ቤት ታተመ።

ኪዳነማሪያም ደምለውና ሌሎች።(1988)። የአዊ ህዝብ አጭር ታሪክ ከአገው ህዝቦች ታሪክ አንጻር። የአዊን ቋንቋ ወደ ጽሁፍ ስርአት ለማሸጋገር በተዘጋጀ ስንፖዚየም የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፣እንጅባራ።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ።(1948)። መጽሀፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሃዲስ።

ዋልተንጉሥ መኮነን።(2007)። ተፈጥሮን መናቅና ሥጋን ማክበር፤ ለክፉ አይን አጋላጭ ክስተት በምሥራቅ ጎጃም በሚገኘው የጎዛምን ማኅበረሰብ እምነት። የአማርኛ ቋንቋ እና ሥነጽሁፍ ፍክሎር ትምህርት ክፍል፣ ለሶስተኛ ዲግሪ የተጠና፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

ጌታቸው ሃይሌ።(1993)።ባህረ ሃሳብ የዘመን ቈጠራ ቅርሳችን ከታሪክ ማስታወሻ ጋር። ሚኖሶታ።

ዚገም ባህልና ቱሪዚም ጽ/ቤት። (2009)።ባህል ቅርስና መስህብ።

Bell, Catherine. (1997).Ritual: Persepectiv and Dimentions. Oxford University Press.

Canda, Edward. (1988).Therautic Transformation in Ritual, and Human Developmnt.

Deborah lipp. (2003). The Elements of Ritual. Printed in United States of America.

Dorson, M. Richard. *Folklore and Folklife: An Introduction*. Published by University of Chicago Press: 1972

Juha, Pentikäinen. (1997). Memorat. In Thomas A Green (Ed), Folklore: an encyclopedia of beliefs, customs, tales, music, and art / edited by Thomas A. Green.

Kyalo, Paul. (2013). Initiation Rites and Rituals in African Cosmology.Mount Kenya University.

Marshal, C. & Rossman, G. (2006).Designing Qualitative Research. United States of America: (4th Ed.). Saga Publication Inc.

Martha, c. Sims and Martine, Stephens.(2005).Living folklore: An Introduction to the Study of people and their Traditions. Utah: Utah State University Press.

Rappaport,Roy.A.(1992).''Ritual.''Folklore,Cultural Performances, and Popular Entertainment. (Ed).Richard bouman. New York: Oxford University Press.

________.(1999). Ritual and Religion in The Making of Humanity. Cambridge University Press.

Segal, Robert. (1980).The myth-Ritualist Theory of Religion.Published by: Black Well.

Thomassen, Bajorn. (2009). The use and meaning of liminality.In International Political Anthropology 2 (1): 5-27.

Thomas Becky L. (2001). The Use of Therapeutic Rituals in Substance Abuse Treatment. UtahState University.

Turner, Victor. (1961).*Ndembu Division Its Symbols & Techniques.* Great Britain; Manchester University Press:

______. (1967).*The Forest of Symbols: Aspects of Ndembu Ritual*.United Kingdom; Cornell University Press:

Tzanelli Ro.danthi (2011). 'Rite of Passage'.University of Leeds Initiation Rites and Rituals in African Cosmology.